በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
TRANSPORT BUREAU

# መንገድን በጊዜያዊነት ዘግቶ ለመጠቀም እና የመንገድ ላይ ኩነት ፈቃድ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2013

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በከተማችን የመንገድ ትራፊክ አደጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን መንገዶችን በጊዜያዊነት ዘግቶ መጠቀም እና የመንገድ ላይ ኩነት ፍላጎቶች በዚያው መጠን እያደጉ በመምጣታቸውየትራፊክ ፍሰትን በማስተጓጎል ለትራፊክ አደጋ መፈጠር መንስኤስለሆኑእነዚህን የመንገድ ላይ ኩነቶች በመቆጣጠርና ስርአት በማስያዝ በመንገድ ተጠቃሚው ዘንድ ተቀባይነት ያለው የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ ኤጀንሲው በርካታ ተግባራትን እያከናወነ የሚገኝ በመሆኑ ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ መንገድ ለመዝጋትና ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ወይም ከታለመለት ዓላማ ውጪ ለመጠቀም ለሚቀርብ ጥያቄ ፈቃድ እንዲሰጥ፣ እንዲያድስ፣ የመንገድ ላይ ኩነቶችን እንዲያስተዳድር እንዲሁም ህግን በሚተላለፉ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ወይም እንዲወሰድ እንዲያደርግ የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት በወጣው በአዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀፅ49 (10) ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣

ይህንን ጥረት ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ኤጀንሲው የሚመራበት የአሰራር መመሪያ ባለመኖሩ መንገድን በጊዜያዊነት ዘግቶ ለመጠቀምና የመንገድ ላይ ኩነቶች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስራዓት ወጥነት እንዲኖረው መመሪያ መምራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት እና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው በአዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 3(ሠ) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጧል፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

#### 1. አጭርርዕስ

ይህ መመሪያ «መንገድን በጊዚያዊነት ዘግቶ ለመጠቀም እና የመንገድ ላይ ኩነት ፈቃድ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2013» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

#### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡

1. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤
2. "ኤጀንሲ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ነው፤

3. "የበላይ አመራር" ማለት የኤጀንሲው ዋናዳይሬክተር ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ማለት ነው፤
4. "ዳይሬክቶሬት" ማለት የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥርና ኩነት አስተዳደርዳይሬክቶሬት ማለት ነው፤
5. " ቡድን " ማለት የመንገድ ትራፊክ ኩነቶች ፈቃድና አስተዳደር ቡድን ነው፤
6. " ቡድን መሪ" የመንገድ ትራፊክ ኩነቶች ፈቃድና አስተዳደር ቡድን የሚመራ ነው፤
7. "ባለሙያ"ማለት በኤጀንሲው የመንገድ ትራፊክ ኩነቶች ፈቃድና አስተዳደር ቡድን ስር ያለ ባለሙያ ማለት ነው፤
8. "መንገድ "ማለትበአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙትን ዋና መንገዶች፣መለስተኛ መንገዶች፣ሰብሳቢ መንገድ፤መጋቢ መንገዶች፣የውስጥለውስጥ መንገዶች፣የመንደር መንገዶች፣ድልድዮችና፣አደባባይ ዙሪያዎች፣መንገድ አካፋይ ደሴቶች፣በመንገዶች ግራና ቀኝ ያሉ የእግረኛና የብስክሌት መተላለፊዎች ያጠቃልላል፤
9. "ፍሰት አዋኪ ቁስ" ማለት ህጋዊ ፍቃድ ሳይኖረው በመንገዶች ላይ የትራፊክ ፍሰትን የሚያስተጓጉሉ ማንኛቸውም ቁስ ነገር ነው፡፡
10." ፈቃድ"ማለት ከኤጀንሲው በመመሪያው መሰረት የተሰጠ መንገድን በጊዜያዊነት ዘግቶ የመጠቀም ወይም የመንገድ ላይ ኩነት ፈቃድ ነው፤
11."ክትትልና ቁጥጥር"ማለትከኤጀንሲው የተሰጠውን ህጋዊ ፈቃድ በአግባቡ ስራ ላይ ማዋሉን ወይም ከኤጀንሲው ፈቃድና ዕውቅና ውጪየሚደረጉ መንገድን በጊዜያዊነት ዘግቶ የመጠቀም ወይም የመንገድ ላይ ኩነት ክትትልና ቁጥጥርነው፤
12."የመንገድ ላይ ኩነት"ማለት በመንገድ ላይ ህጋዊ ፈቃድ ኖሮአቸው በጊዜያዊነት የሚካሄዱ ብሄራዊና ሃይማኖታዊ ባዓላት፣የጎዳና ላይ ስፖርታዊ ውድድሮች፣የንግድ ትርኢትና ባዛር፣ዓውደርዕይ፣ከተሽከርካሪ ነፃ ቀን የሚደረጉ ኩነቶች እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠቃልላል፤
13."ፈቃድ አስተዳደር"ማለት በቡድኑ ውስጥ የሚሰጡ ማናቸውንም የመንገድ ትራፊክ ኩነት ፈቃዶች የመስጠት፣የመከታተልና የመቆጣጠር ሂደት ነው፤
14."የግንባታ ግብዓቶች"ማለት ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ በመንገዶች ላይ የተቀመጡ ፍሰትን የሚያስተጓጉሉአሸዋ፣ ጠጠር፣ድንጋይ፣እንጨት፣አፈር፣ጭቃና መሰል ነገሮችነው፤
15."የግንባታ ተረፈ ምርቶች" ማለት ግንባታዎች ከተጠናቀቁ በኋላ መንገዶች ላይ የተቀመጡፍሰትን የሚያስተጓጉሉ የግንባታ ግብዓት ነዉ፤
16."ሰው"ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸዉ የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

4. ዓላማ

- መንገዶችን በዋናነት ለተሽከርካሪዎች ና እግረኞች ምቹ ሆኖ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ ሠላማዊና ተቀባይነት ያለው የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲረጋገጥ ለማስቻል
- የመንገድ ላይ ኩነቶችአስተዳደርንግልፅናወጥየአሰራር ስርዓት መፍጠርናበመንገድ ተጠቃሚው ዘንድ ፍትሃዊና ተቀባይነት ያለው የመንገድ አጠቃቀም እንዲኖር ማስቻል፤
- ከኤጀንሲዉ ፈቃድ ዉጪ በማናቸዉም ሁኔታ መንገዶችን በጊዜያዊነት ዘግተው የሚጠቀሙትን ተጠያቂ ማድረግ ነው፡፡

5. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሰን ውስጥ በሚገኙ መንገዶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

### መንገድን በጊዚያዊነት ዘግቶ ለመጠቀም እና የመንገድ ላይ ኩነት ፈቃድ ስለሚሰጥባቸው ሁኔታዎች

6. በጊዜአዊነት ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

1/ መንገዶችን ሙሉ በሙሉ በጊዚያዊነት ዘግቶ ለመጠቀም የሚሰጥ ፈቃድ

ሀ.ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ባዕላት

ለ.ስፖርታዊ ውድድሮች

ሐ.ከተሽከርካሪ ነጻ ቀን እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች

2/መንገዶችን በከፊል በጊዚያዊነት ዘግቶ ለመጠቀም የሚሰጥ ፈቃድ

ሀ.ዓውደርዕይ

ለ.የንግድ ትርዒት

ሐ. ባዛርና ኢግዚቢሽን

መ. አዲስና ለመጀመሪያ ጊዜ በሃገር ውስጥ የተሰሩ የፈጠራ ምርቶችን ለማስተዋወቅ

ሠ. የግንባታ ግብዓት /ጠጠር፣ አሸዋ፣ድንጋይ፣አፈር፣ብረትና እንጨት/ በጊዜያዊነት ለማስቀመጥ የሚሰጥ ፈቃድ እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች

3/ ፈቃድ ለማግኘትመሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

ሀ) ለብሔራዊና ሃይማኖታዊ በዓላት ፈቃድ ለማግኘት፤ የፈቃድ ጠያቂው አካል ማመልከቻ ወይም ደብዳቤእናከሚመለከተው አካል የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) ስፖርታዊ ውድድሮችን ለማካሄድ ፈቃድ ለማግኘት፤ የፈቃድ ጠያቂዉ አካል ማመለከቻ ወይም ደብዳቤ እና ከሚመለከተው አካል ኩነቱ እንዲካሄድ የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

ሐ) ከተሽከርካሪ ነፃ ቀን ለማድረግ፤የፈቃድ ጠያቂው አካል ማመልከቻወይም ደብዳቤእናከጤና ቢሮ ወይም ከኤጀንሰዉ የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ፤

መ) ዓውደርዕይ ለማካሄድ ለሚሰጥ ፈቃድ፤የፈቃድ ጠያቂዉ አካል ማመልከቻ ወይም ደብዳቤ እና ከሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ፣ከባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ፣ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፣ከትምህርት ቢሮ፤ከጤና ቢሮ፣ከኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠርያ ጽህፈት ቤት፣ከኢትዮጵያ አምሮአዊ ንብረት ጽህፈት ቤትወይም ከሌሎች ዓውደርዕይ እንዲያካሄድ መፍቀድ ከሚችሉ አካላትየተፃፈ ደብዳቤ፤

ሠ) የንግድትርዒት ለማካሄድ የሚሰጥ ፈቃድ ለማግኘት፣ የፈቃድ ጠያቂዉ አካል ማመልከቻ ወይም ደብዳቤ እናከሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ፣ከባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ወይምከሌሎች ንግድ ትርዒት እንዲያካሄድ መፍቀድ ከሚችሉ አካላት የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ፤

ረ)ባዛርና ኢግዚቢሽንለማካሄድ ፈቃድ ለማግኘት፤የፈቃድ ጠያቂዉ አካል ማመልከቻ ወይም ደብዳቤ እና ከሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ፣ ከባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ወይም ከሌሎች ባዛርና ኢግዚቢሽን እንዲያካሄድ መፍቀድ ከሚችሉ አካላት የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ፤

ሰ)አዲስና ለመጀመሪያ ጊዜ በሃገር ውስጥ የተሰሩ የፈጠራ ምርቶችን ለማስተዋወቅ ለሚሰጥ ፈቃድ፤ የፈቃድ ጠያቂው አካል የማመልከቻ ደብዳቤ እና ከሚመለከተው አካል የፈጠራ ባለቤትነትን የሚገልፅ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሁም የታደሰ ንግድ ፈቃድ፤

ሸ)የግንባታ ግብዓት /ጠጠር፣ አሸዋ፣ድንጋይ፣አፈር፣ ብረትና እንጨት/በመንገድ ላይ በጊዚያዊነት ለማስቀመጥ ለሚሰጥ ፈቃድ፤የፈቃድ ጠያቂው አካል የማመልከቻ ደብዳቤ፣ጊዜው ያላለፈበት የግንባታ ፈቃድ፣ ከግንባታ ዲዛይን ጽህፈት ቤት የግንባታ ግብዓት ማስቀመጫ ምንም አይነትአማራጭ ያለመኖሩንማረጋገጫ ደብዳቤእና ከአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለ ሥልጠን እግረኛ መንገድን ለመጠቀም የተያዘ ውል ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

7. ስለአገልግሎት ክፍያ ሁኔታ

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚሰጥ ፈቃድ ፈቃድ ጠያቂው አካል ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ሀ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፤
2. መንግስታዊ ተቋማት ለሚጠይቁት ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቁም፡፡

8. ፈቃድስለሚሰጥበት ሁኔታ

1. ከላይ በአንቀጽ6(3) በተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት በፈቃድ ጠያቂው አካል የቀረበውን ማመልከቻ ወይምደብዳቤተገቢነቱን ማጣራት ፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሰረት የቀረበው ጥያቄ ተገቢነቱ ሲረጋገጥ የመንገዱን የትራፊክ ፍሰት ሁኔታ በባለሙያዎችየመስክ ምልከታተረጋግጦየውሳኔ ሃሳብለቡድን መሪዉ ይቀርባል፤

ሀ/ ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ የአገልግሎት ክፍያ መክፈሉ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ6 (3) ከፊደል ተራ ሀ/ እስከ ሸ/ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ከ15 ቀን ለማይበልጥጊዜ ፈቃዱይሰጣል

ለ/የፈቃድ ጥያቄው ተቀባይነት ካላገኘ ለፈቃድ ጠያቂው አካል በቃል ወይም በፅሁፍ ምላሽ ይሰጣል

9. ፈቃድስለሚከለከልባቸው ሁኔታዎች

1. በአንቀጽ6 (3) በተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት በፈቃድ ጠያቂው አካልየቀረበው ማመልከቻ ወይም ደብዳቤ ያልተሟላ ሆኖ ሲገኝ
2. የፈቃድ ጥያቄው የቀረበበት መንገድ የትራፊክ ፍሰቱን የሚያስተጓጉል ሆኖ ሲገኝ

10. ፈቃድ የተሰጠዉ አካልየሚጠበቅበት ግዴታዎች

1. በመንገዱ ላይ ለመጠቀም የፈለገበትን ምክንያትና አላማዉን እና ጠቀሜታዉን የሚያስረዳ ጽሁፍ ማቅረብ
2. ለተሰጠው የመንገድ ትራፊክ ኩነት ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል
3. የተሰጠውን የመንገድ ትራፊክ ኩነት ፈቃድ ለታለመለት አላማ ብቻ የማዋል ግዴታ አለበት
4. መንገዱበጊዜአዊነት ተዘግቶእንዲጠቀም ለተሰጠውየፈቃድ አገልግሎትጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑንየሚገልጽ ማመላከቻና ምልክቶችየማስቀመጥና ለህብረተሰቡ የተለየዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የማሳወቅ ሃላፊነት አለበት
5. የፈቃድ ጥያቄዉን ኩነቱ ከሚጀምርበትቀን በፊትከ15 ቀን እስከ አንድ ወርጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲዉ ጥያቄዉን በጽሁፍ ማቅረብ አለበት
6. ከኩነቱ ከተጠናቀቀ በአንድ ቀን ጊዜ ውስጥለኩነቱጥቅም ላይ የዋሉ ማናቸዉም ቁሶችን ከመንገዱ ላይ በማንሳት መንገዱን ለትራፊክ አገልግሎት ክፍት ማድረጉን ለቡድኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት

11. ክትትልና ቁጥጥር

1. ከኤጀንሲው ፈቃድና ዕውቅና ውጪ መንገዶችን በጊዜያዊነት ዘግተው በሚጠቀሙና የመንገድ ትራፊክ ኩነቶችን በሚያካሄዱ አካላት ላይ ኤጀንሲዉ መደበኛና ድንገተኛ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ከዚህ በታች በአንቀጽ12 ከ "ሀ--ረ" የተዘረዘሩትን እርምጃዎች ይወስዳል ወይም እዲወሰድ ያደርጋል፤በሰንጠረዥ " ለ " ስር የተመለከተዉ ቅጣት ተፈጻሚ ይሆናል፡

2. በክትትልና ቁጥጥር ወቅት ከኤጀንሲው የተሰጣቸውን ፈቃድ ከታለመለት አላማ ዉጪ ሲጠቀሙ በተገኙ አካላት ላይ በዚህ መመሪያ ሰንጠንረዥ " ሀ " ስር የተመለከተው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

12. ኤጀንሲዉ ስለሚወስዳቸዉ እርምጃዎች

1. ኤጀንሲውመንገዶችን በመዝጋት ለታለመለት ዓላማ እንዳይዉል ባደረገወይም በዚህ መመሪያ የተከለከሉ ድርጊቶችን ተላልፎ በተገኘ ሰዉ ላይየቃል ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፤

ሀ/ የተዘጉ መንገዶችን የማስከፈት ወይም የትራፊክ እንቅስቃሴ የሚያዉኩና እይታን የሚከለክሉ ማናቸዉንም የፍሰት አዋኪ ቁሶች የማስወገድ ወይም እንዲወገዱ የማስደረግ፤

ለ/ ከኤጀንሲዉ ፈቃድ ዉጪ የግንባታ ግብዓቶችና ተረፈ ምርቶች ፣ አሸዋ፣ ጠጠር፣ድንጋይ፣ ቆርቆርና መሰል ማናቸዉም ነገሮች ከመንገድ ላይ የማስነሳት ወይም የማንሳት፤

ሐ/ ከኤጀንሲዉ ፈቃድ ዉጪ በመንገዶች ላይ የተቀመጡ ጊዚያዊ መጠለያ ወይም የጥበቃ ማደሪያ ቤት ወይም የጥበቃ ማዕከል ወይም በማናቸዉም ሁኔታ መንገዶች ለታለመላቸዉ አገልግሎት እንዳይሰጡ ወይም የመንገድ ትራፊክ ፍሰት የሚያዉኩ ቁሶችን የማንሳት ወይም የማስነሳት ስልጣን አለዉ፤

መ/ከኤጀንሲዉ ፈቃድ ዉጪ በመንገዶች ላይ በዣንጥላ ወይም በማናቸዉም ሁኔታ የንግድ ስራ በሚያከናዉኑ ወይም በተሽከርካሪ የጎዳና ላይ ምርትና አገልግሎት በሚያስተዋዉቁ ወይም የገቢ ማሰባሰቢያ ስራ በሚሰሩ አካላት ላይ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ሠ/ ከኤጀንሲዉ ፈቃድ ዉጪ በመንገዶች ላይ የተቀመጡ ወይም የተከማቹ ወይም የተዘረጉ ድንኳን ፣ሸራ ፣ጥላና መሰል ማናቸዉም ቁሶች ወይም የትራፊክ እንቅስቃሴን ወይም አይታን ሊከልሉ ወይም ሊጋርዱ ወይም ሊያዉኩ ወይም ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ ማናቸዉም ነገሮችን የማንሳት ወይም የማስነሳት ስልጣን አለዉ፤

ረ/ ከኤጀንሲው የተሰጠዉን የመንገድ ትራፊክ ኩነት ፈቃድ ከተፈቀደለት ዓላማ፣ ጊዜና ቦታ ውጪ ተጠቅሞ የተገኘ እንደሆነ ኤጀንሲው የሰጠውን ፈቃድ የመሰረዝ ስልጣን አለው፡፡

2. ድርጊት ፈጻሚዉ ከኤጀንሲዉ በተሰጠዉ ማስጠንቀቂያ መሰረት ፍሰት አዋኪ ቁሶችን ባለማንሳቱ የተዘጋዉ መንገድ ተገቢዉን አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ኤጀንሲዉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12(1)

እና ከፈደል ተራ"ሀ" እስከ "ረ" የተዘረዘሩትን እርምጃዎች ከወሰደ በኋላ ወጪዉን ከድርጊት ፈጻሚዉ በህግ ይጠይቃል፤

3. ከላይ በአንቀጽ 12 (1)ከ "ሀ" እስከ "ረ" የተዘረዘሩትን ተግባራት በሚፈጽምበት ጊዜ እንቅፋት የሆነ ወይም አምባጓሮ የፈጠረ ደንብ ተላላፊአግባብ ባለዉ የወንጀል ህግ ይጠይቃል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ክልከላና ቅጣት

### 13. ክልከላ

1.ማነኛዉም ሰዉ በኤጀንሲዉ ካልተፈቀደለት በስተቀር

ሀ/ መንገዶችን መዘጋትና የግንባታ ግብዓቶችና ተረፈ ምርቶች ፤ አሸዋ ጠጠር ፤ድንጋይ ፤ ቆርቆርናመሰል ማናቸዉም ነገሮችን መንገድ ላይማስቀመጥ ወይም ማከማቸት፤

ለ/ድንኳን ፤ሸራ ፤ጥላና መሰል ማናቸዉም ቁሶች ወይም የትራፊክ እንቅስቃሴንእይታን ሊከልሉ ወይም ሊጋርዱ ወይም ሊያዉኩ ወይም ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ ማናቸዉም ነገሮች ማስቀመጥ ወይም ማከማቸት ወይም መዘርጋት

ሐ) መንገዶችን ዘግቶ ጊዜዊ መጠለያ ወይም የጥበቃ ማደሪያ ቤት ወይም የጥበቃ ማዕከል ማስቀመጥ ወይም በማናቸዉም ሁኔታ መንገዶች ለታለመላቸወ አገልግሎት እንዳይሰጡናየመንገድ ትራፊክ ፍሰት እንዲያስተጓጎል ማድረግ፤

መ) መንገዶችን ዘግቶ በዣንጥላ ወይም በተሽከርካሪ በማናቸዉም ሁኔታየንግድ ስራ ማከናወን ወይም በጎዳና ላይ ምርትና አገልግሎት ማስተዋወቅ ወይም የገቢ ማሰባሰቢያ ስራ ማካሄድ

ሠ/ የተሰጠዉን የመንገድ ትራፊክ ኩነት ፈቃድ ከተፈቀደለት ጊዜ ፤ዓላማናከተፈቀደዉ ቦታ ዉጪ ማዋል የተከለከለ ነዉ፤

### 14. ቅጣት

ማንኛውም ሰዉ ከላይበአንቀፅ12የተዘረዘሩ ክልከላዎችን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በአንቀፅ 13የተደነገገ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነውፈቃድ በተሰጠው አካል ላይ በሰንጠረዥ " ለ"እና "ሐ" የተመለከቱት ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

15.የቅጣት አፈፃፀም

1. ኤጀንሲዉ ጥፋት ፈጽሞ በተገኘ ማናቸዉም አካል ላይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 የተመለከተውን እርምጃ በመዉሰድ ከጥፋቱ የማይታረም አካል ላይ ላጠፋው ጥፋት የቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

2... ጥፋት ፈፅሞ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም አካል የቅጣት ክፍያውን በመንገድ ትራፊክ ቁጥጥርና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ገንዘብ ማሰባሰቢያ ስርዓት መሰረት ክፍያ ይፈፅማል፡፡

3. በዚህ መመሪያ አንቀፅ15ንዑስ አንቀፅ አንድና ሁለት የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ህግ አስከባሪ አካላት የመመሪያው አስፈፃሚ ናቸው፡፡

4. በዚህ መመሪያ ስልጣን የተሰጣቸዉ አስፈፃሚ አካላት ይህን መመሪያ በመተላለፍ ጥፋት ፈፅመው የተገኙ ደንብ ተላላፊዎችየቅጣት ክፍያ እንዲፈፅሙያደርጋሉ፡፡

5.በዚህ መመሪያ የቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት ተቆርጦለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቅጣቱን መፈፀም ያልቻለ ማንኛውም ሰዉከሌሎች ህግ አስከባሪ አካላት ጋር በመተባበር በቅንጅት እንዲከፍልይደረጋል፡፡

6. በዚህ መመሪያ አንቀጽ15 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የተጣለበትን ቅጣት መፈፀም ያልቻለ ማንኛውም ሰዉዳይሬክቶሬቱ በሚያስተላልፈዉ መረጃ መሰረት በኤጀንሲዉ ህግ ዳይሬክቶሬት አማካኝነት አግባብ ባለው ህግ እንዲጠየቅና እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

16 .ስለ ቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ

1. ይህንን መመሪያ ተላልፎ ቅጣት የተጣለበት እና ቅሬታ ያለው ሰው ቅጣት ከተጣለበት ቀን ጀምሮ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን በፅሁፍ ያቀርባል የቀረበውን አቤቱታ በአምስት ቀንውስጥ የውሳኔ ሃሳብ ለኤጀንሲው የበላይ ሃላፊ ያቀርባል፤

2. ቅሬታ የቀረበለት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በአምስት የስራ ቀናት

3. የኤጀንሲው የበላይ ሀላፊ ከቅሬታ ሰሚኮሚቴዉ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው ዉሳኔዉን በፅሁፍ ያሳውቃል፡

4. በኤጀንሲው የበላይ ሃላፊ ውሳኔ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢውሳኔው በደረሰው በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በጽሁፍ ለትራንስፖርት ቢሮ ሃላፊ ያቀርባል፡፡ የቢሮ ሃላፊው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17.የመተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡

### 18.መመሪያውን ስለማሻሻል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን የአፈጻጸም መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል፡፡

### 19.መመሪያውን ስለማስፈጸም

የአዲስ አበባ መንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ይህን መመሪያ እንዲያስፈፅም ሃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

### 20.የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ቀብ ጀምሮ ተፈፃሚይሆናል፡፡

<u>ሠንጠረዥ ሀ</u>

<u>የአገልግሎት ክፍያ ተመን</u>

| ተ.ቁ | የአገልግሎት/ፈቃድ/ አይነት | የአገልግሎት ክፍያ ተመን |
|---|---|---|
| 1 | የተጠየቀው ፈቃድ የሚሸፍነው ቦታ 1 ሜትር በአንድ ሜትር ሆኖ እስከ 1 ቀን ለሚዘልቅ ቆይታበቀን | ብር 1000.00 |
| 2 | የተጠየቀው ፈቃድ የሚሸፍነው ቦታ 1 ሜትር በአንድ ሜትር ሆኖ እስከ 10 ቀን ለሚዘልቅ ቆይታ በቀን | ብር 1500.00 |
| 3 | የተጠየቀው ፈቃድ የሚሸፍነው ቦታ 1 ሜትር በአንድ ሜትር ሆኖ ከ10 ቀን በላይ ለሚዘልቅ ቆይታ በቀን | ብር 2000.00 |
| 4 | የግንባታ ግብዓት እና ተረፈ ምርት ለማስገባት እና ለማስወጣትና ለአንድ ቀን | ብር 5000.00 |

## ሰንጠረዥ ለ.

## የቅጣት ሠንጠረዥ

ፈቃድ ወስዶ ከታለመለት ዓላማ ወይም ከተሰጠዉ ጊዜ በላይ ከተፈቀደለት መጠንና ቦታ ዉጭ የተጠቀመ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት/ፈቃድ/ አይነት | የጥፋት ዓይነት | የቅጣት መጠን በብር |
|---|---|---|---|
| 1 | ዓወደርዕይ፣ የንግድ ትርዒት፣ ባዛርና ኢግዚቢሽን፣ የፈጠራ ምርቶች ፈቃድ | ፈቃድ ሳይጠይቅ የተጠቀመ | 10000.00 |
| | | የፈቃድ ቀን አሳልፎ የተጠቀመ ለቀን | 10000 |
| | | ከተፈቀደው የድንኳን ቁጥር በላይ የተከለ | ለእያንዳንዱ ድንኳን ለቀን 200.00 |
| | | ከተፈቀደው መንገድ ውጪ ድንኳን የተከለ | 10000.00 |
| | | ፈቃዱን ከተሰጠው ዓላማ ውጪ የተጠቀመ | 10000.00 |
| | | የተሰጠውን ፈቃድ ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ | 10000.00 |
| 2 | የግንባታ ግብዓት /ጠጠር፣ አሸዋ፣ድንጋይ፣አፈር፣ ብረትና እንጨት/በጊዜያዊነት በመንገድ ላይ ያስቀመጠ | ያለፈቃድ ያስቀመጠ | 20000.00 |
| | | የፈቃድ ቀን አሳልፎ የተጠቀመ በቀን | 10000.00 |
| | | ከተፈቀደው የመንገድ ውጪ ያስቀመጠ | 5000.00 |
| | | ፈቃዱን ከተሰጠው ዓላማ ውጪ የተጠቀመ | 500.00 |
| | | ከተፈቀደው የመንገድ ስፋት በላይ የተጠቀመ | 500.00 |
| | | የተሰጠውን ፈቃድ ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ | 500.00 |

**ሐምሌ 2012**

**አዲስ አበባ**

ስጠታው አካለ ጥላዬ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ